etnetsa apps™

# የET ነፃ ዲጂታል ሳንቲም ($ETN) እቅድ [WHITE PAPER]

ቅፅ 1.1

©etnetsa apps , 2024
All Rights Reserved

© Identico, 2024
All Rights Reserved

Identico®

Mickey Leland St.
Bole Atlas, Isabella Building, 3rd Floor
Addis Ababa, Ethiopia

Contact Us
+251 96 556 4436
identicostudio@gmail.com

# 1. መግቢያ

እንኳን ወደ ET Netsa AppsTM የኮሚዩኒቲ ፕሮጀክት መገልገያ ዲጂታል ኮይን ወደሆነው የ ET Netsa Coin ($ETN) እቅድ መግለጫ በደህና መጡ። ይህ ሰነድ በዋነኝነት ስለ$ETN ቶክን ዋነኛ ጥቅም፤ ለምን ሊፈበረክ እንደቻለ፤ ስለቶክኑ ምጣኔ ሀብታዊ ሁነትና የET Nesta ኮሚዩኒቲ አባላትም ሆኑ በዘርፉ ላይ የሚሳተፉ መላው ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በአገራችን በአይነቱ የመጀመሪያ በሆነው በዚህ የዲጂታል እሴት ፕሮጀክት ላይ ሊሳተፉና ሊጠቀሙ ስለሚችሉባቸው ሁነቶች የሚገልፅ ፅሁፍ ነው።

# 2. የፕሮጀክት መግለጫ

ET Netsa Coin ($ETN) በኮሚዩኒቲ እሳቤ ላይ የታነፀና እንቅስቃሴዎቹንም በጋራ ትብብር እና መተጋገዝ ላይ ያደረገ ፕሮጀክት ነው። ፕሮጀክቱ በዋነኝነት ይፋ የሆነበት የመጀመሪያ መነሻ ሀሳብም በኢትዮጵያ ያሉ የክሪፕቶ ተገበያዮች ዲጂታል አሴቶችን በመያዝ፤ በመግዛት እና በመሸጥ ሂደት ውስጥ ያሉትን መሰረታዊ ክንውኖች ከስረ መሰረታቸው ግልፅ እና ጥልቅ በሆነ መንገድ እንዲረዱት ሲሆን በቀጣይ ፕሮጀክቱ የተጠቃሚዎቹ ቁጥር በሰፋና ባደገ ቁጥርም ሌሎች ሰፋፊ የክሪፕቶና የብሎክቼይን ትምህርታዊ ሀሳቦችን አንግቦ የተነሳ ፕሮጀክት ነው። በተለይም መነሻ ሀሳቡን መሬት ላይ አውርዶ ለመተግበር በቴሌግራም የቀጥታ ስርጭቶች አማካኝነት የገበያ ውስጥ እንቅስቃሴዎች ለምን እና በምን ሁነት ተፅእኖ እንደሚያርፍባቸው ይህንኑ ኮሚዩኒቲው በራሱ የመሰረተውን ኮይን በመጠቀምና ግብይት ላይ የሚውለውን የገንዘብ መጠንም የኮሚዩኒቲው አባላት በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የነፍስ ወከፍ የፕሮጀክር እርዳታ በማድረግ ስለክሪትቶ ግብይቶች ተግባራዊ ትምህርትን ለመስጠት የመጣና እግረመንገዱንም ስለብሎክቼይን ምንነትና መሬት ላይ በወረደ የቤተ ሙከራ እንቅስቃሴ ስለሴክተሩ የበለጠ እውቀትን ለማስፋፋት እቅዱን አርጎ የተነሳ ፕሮጀክት ነው። ይህም በዋነኝነት ኮሚዩኒቲያችን የተለያዩ የገበያ ሁነቶች ያላቸውን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅእኖዎች ለይተው እንዲያውቁትና በተጨባጭም እውቀትን እንዲቀስሙበት የታለመ አፈፃፀም ነው።

©etnetsa apps , 2024
All Rights Reserved

© Identico, 2024
All Rights Reserved

Mickey Leland St.
Bole Atlas, Isabella Building, 3rd Floor
Addis Ababa, Ethiopia

Contact Us
+251 96 556 4436
identicostudio@gmail.com

# 3. የቶክን ምጣኔ ሀብት [TOKENOMICS]

አጠቃላይ የቶክኑ የአቅርቦት መጠን ፡

## የ$ETN ቶክን አጠቃላይ ብዛት በጠቅላላው 5,000,000 ቶክኖች ይሆናል።

### የቶክን ስርጭት

**ኤርድሮፕ**

1,000,000 የ$ETN ቶክኖች በኤርድሮፕ አማካኝነት ለኮሚዩኒቲው አባላት በሽልማት መልክ የሚሰጥ ሲሆን ይህም በዋነኝነት የቶክኑን ተደራሽነት እና የተጠቃሚዎች ቁጥር ለመጨመር የሚረዳ እንዲሆን ታቅዶ የተዘጋጀ ሁነት ነው።

**ሊውኪዲቲ ፑል(LP)**

2,000,000 የ$ETN ቶክኖች እኩል የዋጋ መጠን ካላቸው የTON ቶክኖች ጋር በማጣመር ወደ ሊውኪዲቲ ፑል የሚጨመሩ ይሆናል። ይህም በዋነኝነት ቶክኑ የሊውኪዲቲ/የግብይት ችግር እንዳይገጥመው እና በተጨማሪነትም በኢማእከላዊ የመገበያያ ፕላትፎርሞች ላይ ለግብይት ለመቅረብ የሚያስችለው ይሆናል።

**Tonraffel Fairlaunch ላይ የሚደረግ የቅድመ-ሽያጭ[Pre-sale]**

1,000,000 የ$ETN ቶክኖች ደግሞ ምናልባትም ሌሎችይ የJetton ፕሮጀክቶች ሲያደርጉት በማይስተዋለው መንገድ መቶ በመቶ የቅድመ ሽያጭ ገቢው በቀጥታ ቶክኑ በኢማእከላዊ ኤክስቼይንጅ ላይ ሲመዘገቡ ወደሊውኪዲቲ ፑሉ የሚጨመሩ ይሆናል። ይህ የቶክን ቅድመ ሽያጭ አካሄድ አባልት አስቀድመው በዚህ የፕሮጀክቱ ደረጃ ላይ የሚገዙትን ቶክኖች አትርፈው እንዲሸጡ የሚያስችላቸውን እድል ከመስጠቱ ባለፈ ለቅድመ ሽያጩ የሚዘጋጀውን ሊንክ በመጠቀም በአባላቱ በኩል የሚመጡ አዳዲስ ተጠቃሚዎች ሲኖሩ እነዚህ አዳዲስ ገበዎች ከሚያዋጡት የTON ቶክኖች ላይ የኮሚሽን ክፍያን የሚያገኙበት ሁነት የሚመቻችበት ይሆናል።

**ለፕሮጀክቱ አበልፃጊዎች [Developers] ቡድን ተቆልፎ የሚቀመጥ ተቀማጭ**

1,000,000 የ$ETN ቶክኖች ለፕሮጀክቱ የወደፊት እንቅስቃሴዎች እና ተግባራት ጥቅም ላይ እንዲውል የማይንቀሳቀስ ተቀማጭ ሆኖ የሚቀመጥ ይሆናል። ይህም ፕሮጀክቱ በሚኖሩበት በጋራ የመስራት ስምምነቶች፤ የማስታወቂያ ስራዎች፤ የሶፍትዌር ማበልፀግ ሂደቶች እና ለኮሚዩኒቲው ማነሳሻ ለሚሆኑ የተለያዩ ወጪዎች የሚውል ይሆናል።

©etnetsa apps , 2024
All Rights Reserved

© Identico, 2024
All Rights Reserved

Identico®
Mickey Leland St.
Bole Atlas, Isabella Building, 3rd Floor
Addis Ababa, Ethiopia

Contact Us
+251 96 556 4436
identicostudio@gmail.com

## የሊውኪዲቲ ፑሉ ትግበራ ማብራሪያ

በአጠቃላይ የፕሮጀክቱ ሊውኪዲቲ ፑል 2,000,000 የ$ETN ቶክኖችን ከ200 የ$TON ቶክን ጋር በማጣመር የሚይዝ ይሆናል። ይህ ጥምረት በዋነኝነት የ$ETN ቶክን መነሻ የመመዘኛ ዋጋ እንዲኖረው የሚረዳ ይሆናል። ሂሳባዊ ስሌቱ የሚከተለውን ይመስላል፡

### አጠቃላይ በፑሉ ውስጥ የሚኖረው የቶክን ብዛት

| $ETN | TON |
|---|---|
| 2M ቶክኖች | 200 ቶክኖች |

# 4. የቶክኑ ትግበራዊ ሁነት [Use Case]

የ$ETN ቶክን በዋነኝነት በET Netsa Apps™ ስርዓተ ምህዳር ውስጥ ለተለያዩ አገልግሎቶች ጥቅም ላይ የሚውል ይሆናል። ዋና ዋና ጥቅሞቹም :

### ለግብይት አፈፃፀም የሚውሉ ክፍያዎች [Transaction Fees]:

ተጠቃሚዎች በአፕሊኬሽኑ ውስጥ ለሚያገኛቸው የተለያዩ አገልግሎቶች ክፍያን በሚፈፅሙበት ሁነት ለክፍያዎቻቸው ማስፈፀሚያነት እንደትራንዛክሽን ክፍያ ያገለግላሉ። Users can pay for transactions within the app using $ETN.[needs Citation]

### ለማበረታቻ ሽልማቶች

በኮሚዩኒቲው ውስጥ በሚኖራቸው የተሳታፊነት ልክ ከሌላው በይብለጥ ጠንክረው ለሚሳተፉ ተጠቃሚዎች ለሚውሉ የተለያዩ ማበረታቻ ሽልማቶችነት ጥቅም ላይ ይውላል።

### ስቴክ ለማድረግ

የ$ETN ቶክንን ስቴክ የሚያደርጉ ተጠቃሚዎች ለሚኖራቸው ድርሻ የተለያዩ ክፍያዎች እና ሽልማቶችን በአፕሊኬሽኖች ውስጥ ለመከወን ጥቅም ላይ ይውላሉ።

### የቶክን መስተጋብራዊ ክፍልፋይ

በሊውኪዲቲ ፑሉ ውስጥ የሚገኘው የ$ETN ቶክን ከ$TON ቶክን ጋር ያለው ሚዛናዊ ክፍልፋይ የሚከተለውን

### የ$ETN ቶክን ዋጋ መመዘኛ

አንድ የ$ETN ቶክን ሊያወጣ የሚችለውን የዋጋ ተመን ለማወቅ በፑሉ ውስጥ ያለውን አጠቃላይ የ$TON ቶክኖች ብዛት በአጠቃላይ ካለው የ$ETN ቶክኖች ጋር በማካፈል ማግኘት የምንችል ይሆናል። ይህም በዋነኝነት አንድ የ$TON ቶክን ከእያንዳንዱ የ$ETN ቶክን ጋር ያለውን የዋጋ ተመን እንድናውቅ የሚረዳን ይሆናል። ሂሳባዊ ቀመሩም የሚከተለውን

$$\text{Valuation of 1 \$ETN} = \frac{200 \text{ TON}}{2,000,000 \text{ ETN}} = \frac{200}{2,000,000} \text{ TON} \text{Valuation of 1 \$ETN} = \frac{1}{10,000} \text{ TON}$$

በዚህም አማካኝነት ከጅምሩ የሚኖረው የአንድ $ETN ቶክን ዋጋ የአንድ $TON ቶክንን ዋጋ 1/10,000ኛ መጠን የሚይዝ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህም ማለት አንድ የ$ETN ቶክን ከ0.0001 $TON ቶክን ጋር እኩል የምጣኔ መጠን ልኬት ይኖረዋል ማለት ነው።

©etnetsa apps , 2024
All Rights Reserved

© Identico, 2024
All Rights Reserved

Identico®
Mickey Leland St.
Bole Atlas, Isabella Building, 3rd Floor
Addis Ababa, Ethiopia

Contact Us
+251 96 556 4436
identicostudio@gmail.com

# 5. የኮሚዩኒቲው ተሳታፊነት

የኮሚዩኒቲያችን አባላት በET Netsa Coin ፕሮጀክት ላይ የልብ ትርታና ዋነኛ ባለድርሻ አካላት ይሆናሉ። ከ26 ሺህ በላይ አባላት ባሉት በዚህ ጠንካራ ኮሚዩኒቲ አገዛ እና አብሮ የማደግ ተነሳሽነትም እጅግ የጠነከረ የኮሚዩኒቲ ባህል እና እንቅስቃሴም እንደሚኖረው እሙን ነው። በዋነኝነት የአባላትን ተሳታፊነት እና ባለድርሻ አካልነት ለማረጋገጥም ፕሮጀክቱ ካቀዳቸው እቅዶች መካከል በቴሌግራም የላይቭ መድረኮች አማካኝነት ስለገበያ እንቅስቃሴዎች በቀጥታ በሚዘጋጁ መርሀ ግብሮች ስለአጠቃላይ የክሪፕቶ ከረንሲ የግብይት ምህዳሩ መማማርን ጨምሮ በሰዓቱ የሚኖሩ የመግዛትና የመሸጥ፣ የስትራቴጂ፣ የኢንቨስትመንት እና የቀን ተቀን ግብይት ሁነትን ያማከለ የትሬድ ሲግናልን የሚያገኙበት ሁነት የሚመቻች ይሆናል። ይህም ኮሚዩኒቲው በአጠቃላይ በሚኖረው እንቅስቃሴ ላይ ግልፅ የሆነና የተሳታፊዎች እንቅስቃሴም የተጠናከረ እንዲሆን ያደርገዋል። በተጨማሪነትም አባላት የራሳቸው የሆነ የገቢ ማግኛ መንገድ ከመቅረፅ ባለፈ በትሬዲንግ አለም ያለውን ሁነት በቀላሉ እንዲረዱት ወደፊት በሚኖራቸው በመስኩ የሚደረግ እንቅስቃሴም ስኬታማ እንዲያደርጋቸው ታስቦ የታቀደ ሁነት

# 6. ፍኖተ ካርታ

**ምዕራፍ አንድ :**
የቶክን ስራ ጅማሬ [Launch]

- 1,000,000 የ$ETN ቶክኖችን የያዘ ኤርድሮፕ ለተሳታፊዎች ማከፋፈል።
- 2,000,000 የ$ETN ቶክኖችን እና 200 የ$TON ቶክኖችን የያዘ ሊውኪዲቲ ፑሉ ማዘጋጀት።
- የ1,000,000 $ETN ቶክኖችን የቅድመ ሽያጭ[Pre-sale] ማስጀመር።

**ምዕራፍ ሁለት :**
የአፕሊኬሽን ማበልፀግ ሂደት

- የ$ETN ቶክንን በET Netsa Apps™ አፕሊኬሽን ላይ ለትራንዛክንሽ ክፍያዎች እና ለተለያዩ የማበረታቻም ሆነ የክፍያ አካሄዶች ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ።
- የ$ETN ቶክንን የያዙ ተጠቃሚዎች የስቴኪንግ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁነት ማመቻቸት።
- የ$ETN ቶክን አገልግሎት ላይ የሚውልበትን ሁነት ለማመቻቸትና ለማሳለጥ ይረዳ ዘንድ የተለያዩ በጋራ የመስራት ስምምነቶችን ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ጋር መፈፀም።

**ምዕራፍ ሶስት :**
እድገት

- የተለያዩ ኢቬንቶችና ፕሮሞሽኖችን በማድረግ ኮሚዩኒቲው ሰፊ ተደራሽነት እንዲኖረውና የአባላት ቁጥሩም እንዲጨምር እና እንዲጠናከረ እንቅስቃሴዎች ማድረግ።
- የ$ETN ቶክን ተጨማሪ የኢማእከላዊ መገበያያ ፕላትፎርሞች ላይ እንዲመዘገብ በማድረግ ሊውኪዲቲው እንዲጨምርም ሆነ የተለያዩ የመገበያየት እድሎች እንዲኖሩ ማድረግ።
- ET Netsa Apps™ የአፕሊኬሽን ምህዳረ ስርዓት ላይ የተለያዩ ጥቅም የሚሰጡ የፈጠራ ኹነቶችንና የመጠቀሚያ አገልግሎቶችን በመጨመር አገልግሎቱን ማስፋት።

©etnetsa apps , 2024
All Rights Reserved

© Identico, 2024
All Rights Reserved

Identico®
Mickey Leland St.
Bole Atlas, Isabella Building, 3rd Floor
Addis Ababa, Ethiopia

Contact Us
+251 96 556 4436
identicostudio@gmail.com

# 7. የJETTON ስማርት ኮንትራክት ከመታገዱ በፊት ሊከወን የሚችል ፕሮፖዛል

በአንድ መገበያያ ምጣኔ ሀብታዊ ሁነት ውስጥ ለመገበያያነት የሚቀርበው የገንዘብ ብዛት መጠን አነስተኛ አቅርትቦት ሲኖረው መገበያያው በዋጋ ደረጃ የተሻለ አቅም እና ምዘና እንደሚኖረው እሙን ነው። ይህ ምጣኔ ሀብታዊ ሁነት በ$ETN ቶክን ላይም ይተገበር ዘንድ ከዚህ በፊት በክሪትቶ ምህዳሩ የቶክኖቻቸውን ምዘና በመሰል አካሄዶች ከቀየሱ የክሪፕቶ ፕሮጀክቶች በመውሰድ ቶክኑ በረጅም ጊዜ እንቅስቅሴው እና የወደፊት እድገቱ ላይ እገዛን ሊያደርግለት አሰራርን መጨመር የሚቻልበት ሁነት ይኖራል። ለዚህም እንደማሳያነት የ$ShibaInu ቶክን ሺባሪየም በተሰኘው አሰራሩ እንዴት ቶክኖቹ ወደፊት በሚኖራቸው እንቅስቃሴ የዋጋ ግሸበታቸውን መቀነስ እንደሚቻል በማጥናት የ$ETN ቶክንም በጊዜ ሂደት በነባራዊው አለም ያለውን የመገበያያ ኖቶች ግሸበት ሊያሸንፍ እንደወጠነ እንመልከት።

ይህን ትግበራ ፕሮጀክቱ ከዳር በሚያደርስበት ወቅት የግሸበት መጠኑን ለመቆጣጠር እና በሂደት ከሚኖሩ የዋጋ መገሸብ ሁነቶች ጥበቃን እንዲያገኝ እያንዳንዱ በቶክኑ አማካኝነት የሚደረጉ ግብይቶች ወይም የቶክን ዝውውሮች በሚደረጉበት ወቅት እጅግ በጣም አነስተኛ የሆነ የመቶኛ ድርሻው ላይ ተቀንሶ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ቶክኖቹ የሚቃጠሉበት እና ከአገልግሎት ውጪ የሚሆኑበት አሰራር ይሆናል። ይህም አስቀድሞ እንደተቀመጠው እና በመሰረታዊ የኢኮኖሚክስ ትምህርቶች እንደአንድ ፅንሰ ሀሳብ የሚቀርበውን የአንድ እሴት አቅርቦት በሚቀንስበት እና ፍላጎቱ የነበረበት ሁነት ላይ አልያም ጭማሪን በሚያሳይበት ወቅት አጠቃላይ ያለው ዋጋ እንዲያድግ የሚያደርገው ይሆናል። ይሁንና ይህ ውሳኔ እጅግ ጠንካራ እና ከፍ ያለ ቦታ የሚሰጠው እንደመሆኑ፤ ጎን ለጎንም ፕሮጀክቱ የኮሚዩኒቲው የሆነና በኮሚዩኒቲው ሀሳቦችና ድምፅ ላይ የተመሰረተ አካሄድን እንደመምረጡ አካሄዱን ሙሉ ለሙሉ ግልፅ እና ዲሞክራሲያዊ ለማድረግ ሲባልም ጭምር በዚህ ፕሮፖዛል ላይ አሁን ላይ ያለው የጄተን ስማርት ኮንትራክት ባለቤትነት ከመወገዱ በፊት በዚህ የአሰራር ለውጥ ላይ ኮሚዩኒቲው ድምፅ የሚሰጥበት የሚሆን ይሆናል። ይህ ትግበራ የሚኖረውን ትግበራ ቴክኒካዊ በሆነ ሁነት ለመግለፅ ያህል ከዚህ በታች የተቀረፀበትን የ[Tact] funC ኮድ በሚከተለው መልኩ ቀርቧል።

## ሽፍሽፋዊ [DEFLATIONARY] የJETTON ኮንትራክት በTACT ኮድ

ከዚህ በታች በTACT የፕሮግራም ቋንቋ ላይ የተመሰረተውን ፀረ-ግሸበታዊ የቶክን ኮንትራክት ኮድ መመልከት ይቻላል።

```
pragma ton-solidity ≥ 0.39.0;

contract DeflationaryJetton {
    // Declare state variables
    uint256 public totalSupply;
    mapping(address ≥ uint256) public balanceOf;

    // Constants for fee and burn percentage
    uint8 public constant FEE_PERCENTAGE = 1;
    uint8 public constant BURN_PERCENTAGE = 50;

    // Event declarations (if supported)
    event Transfer(address indexed from, address indexed to, uint256 value);
    event Burn(address indexed burner, uint256 value);

    // Constructor to initialize the contract with an initial supply
    constructor(uint256 initialSupply) public {
        totalSupply = initialSupply;
        balanceOf[msg.sender] = initialSupply;
    }

    // Internal function to handle transfers and fees
    function _transfer(address _from, address _to, uint256 _value) internal {
        require(_to != address(0), 101); // Invalid address error code
        require(balanceOf[_from] ≥ _value, 102); // Insufficient balance error code

        uint256 fee = (_value * FEE_PERCENTAGE) / 100;
        uint256 burnAmount = (fee * BURN_PERCENTAGE) / 100;
        uint256 remainingFee = fee - burnAmount;
        uint256 amountToTransfer = _value - fee;

        balanceOf[_from] -= _value;
        balanceOf[_to] += amountToTransfer;
        totalSupply -= burnAmount;

        emit Transfer(_from, _to, amountToTransfer);
        emit Burn(_from, burnAmount);
    }

    // Public function to transfer tokens
    function transfer(address _to, uint256 _value) public {
        _transfer(msg.sender, _to, _value);
    }
}
```

©etnetsa apps , 2024
All Rights Reserved

© Identico, 2024
All Rights Reserved

Identico®
Mickey Leland St.
Bole Atlas, Isabella Building, 3rd Floor
Addis Ababa, Ethiopia

Contact Us
+251 96 556 4436
identicostudio@gmail.com

በቀረበው የስማርት ኮንትራክት ላይ 10,000 የ$ETN ቶክኖችን ለመላክ በምንፈልግበት ወቅት ኮንትራክቱ ከዚህ ግብይታችን ላይ የግብይት መፈፀሚያ ክፍያን እና በመቶኛ ከተሰላው ሂሳባዊ ስሌትም በመነሳት ለግሽበት መቆጣጠሪያ ያገለግላል የተባለውን የቶክን መጠን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ተመልሶ ግልጋሎት ላይ እንዳይውል አድርጎ የሚያቃጥለው ይሆናል። የትግበራውን ሁነት አንድ በአንድ ለመመልከት ያህልም :

## የመጀመሪያ ደረጃ ሁነት [SETUP]: 01

- ኮንትራክቱ አጠቃላይ የቶክኖችን ድምር ቁጥር የያዘ ነው።
- balanceOf የሚለው ኮድ እያንዳንዱ አድራሻ ያለውን አጠቃላይ የቶክን መጠን የሚገልፅ ነው።
- የግብይት መፈፀሚያ ክፍያን(FEE_PERCENTAGE) የአጠቃላይ ክፍያው አንድ መቶኛ ይሆናል።
- የሚቃጠለው(BURN_PERCENTAGE) የቶክን ብዛት በመቶኛ ከተቆረጠው የክፍያ መፈፀሚያ 50 በመቶው ይሆናል።

## የማስተላለፍ ሁነትን መፈፀሚያ ትእዛዝ [FUNCTION:] 02

- transfer(address _to, uint256 _value) የሚለው ማዘዣ ኮድ የሚጠራበት እና በፕሮግራሙ ውስጥ ተግባራዊ የሚሆነው 10,000 የ$ETN ቶክኖችን ለማስተላለፍ ነው።
- _value አጠቃላይ ለዝውውር የቀረበው የቶክን መጠን የሚገልፅ ሲሆን በምሳሌያችንም 10,000 የ$ETN ቶክኖች ይሆናል።

## የግብይት መፈፀሚያ ክፍያ ሂሳባዊ ስሌት [Transaction Fee]: 03

- የግብይት መፈፀሚያ መጠኑ ከአጠቃላይ የሚተላለፈው የቶክን መጠን አንድ መቶኛው ይሆናል። =\text{fee} =

## የሚቃጠሉ የቶክኖች ብዛት ሂሳባዊ ስሌት 04

- የሚቃጠለው የቶክን ብዛት ከአጠቃላይ የግብይት መፈፀሚያ የቶክኖች ብዛት[Txn Fee] 50 በመቶ ያህሉ ይሆናል።

## ከማቃጠል ሁነቱ በኋላ የሚኖረው የግብይት ክፍያ መጠን: 05

- ከግብይት መፈፀሚያ ክፍያው ላይ የተቃጠለውን የቶክን ብዛት በመቀነስ ለግብይት ማድረጊያነት አገልግሎት ላይ የሚውለውን የትራንዝክሽን መፈፀሚያ የቶክን መጠን

## የሚተላለፈ የቶክኖች መጠን : 06

- በቶክን ዝውውሩ ተቀባዩ የሚቀበለው የቶክኖች ብዛትን ለማግኘት ደግሞ ላኪው ከላከው አጠቃላይ የቶክኖች ብዛት ላይ ለግብይት መፈፀሚያነት የተቆረጠውን እና በግብይት ሁነቱ የተቃጠሉትን የቶክኖች ብዛት በመቀነስ ማወቅ የሚቻል ይሆናል።

=\text{amountToTransfer} = \text{_value} - \text{fee} = 10,000 - 100 = 9,900 \, \text{$ETN}

## ቀሪ ሂሳብን በአዲስ መልክ የመመዝገብ ሁነት : 07

- ግብይቱ ከተፈፀመ በኋላ ከላኪው ቀሪ ሂሳብ ላይ 10,000 የ$ETN ቶክኖች ተቀናሽ የሚሆኑ ይሆናል። (_value = 10,000 $ETN).
- የተቀባዩ ቀሪ ሂሳብ በተላከው እና የግብይት መፈፀሚያ እና የግሽበት መቆጣጠሪያ የቶክን ቅነሳ ከተደረገበት በኋላ 9,900 የ$ETN ቶክኖች የሚጨመሩለት ይሆናል።
- በግብይት ሂደቱ ለግሽበት መቆጣጠሪያነት ታስቦ የሚቃጠለው የቶክኖች ብዛት 50 የ$ETN ቶክኖች ሲሆኑ ይህም የቶክኖች ቁጥር ግብይቶች በተፈፀሙ ቁጥርና ቶክኖቹ በተቃጠሉ ቁጥር ከአጠቃላይ የቶክኑ የአቅርቦት ቁጥር ላይ የሚቀነሱ ይሆናል።

## የተብራራ ተግባራዊ ምሳሌ:

ለምሳሌ እንበልና :

የላኪው የመጀመሪያ ቀሪ ሂሳብ

**20K $ETN**

የተቀባይ የመጀመሪያ ቀሪ ሂሳብ

**5K $ETN**

ቶክኑን እንዲያስተላልፍ ለስርዓተ መረቡ transfer(recipientAddress, 10,000) የሚለውን ትእዛዝ ስንፈፅም:

**01**

የላኪ ቀሪ ሂሳብ =

20,000 - 10,000 = 10,000 \, \text{$ETN}

**02**

የተቀባዩ ቀሪ ሂሳብ =

5,000 + 9,900 = 14,900 \, \text{$ETN}

**03**

የሚቃጠለው የቶክኖች ብዛት =

50 \, \text{$ETN}

**04**

ከአጠቃላይ የቶክን አቅርቦቱ ላይ የሚቀነሰው የቶኖች ብዛት=

totalSupply=totalSupply-50\text{totalSupply} = \text{totalSupply} - 50totalSupply=totalSupply-50

በሂደቱ የሚደረጉ ሁነቶች :

- Transfer የተሰኘው ትእዛዝ 9,900 ቶክኖች ከላኪው ወደ ተቀባዩ አድራሻ ቶክኖቹ እንዲዘዋወር የሚያደርግ ይሆናል።
- Burn የተሰኘው ትእዛዝ ደግሞ ከላኪው ቀሪ ሂሳብ ላይ 50 ቶክኖች ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲቃጠሉ እና ከአገልግሎት ውጪ እንዲሆኑ የሚያደርግ ይሆናል።

## ማጠቃለያ:

| የተላከው ጠቅላላ መጠን | የተቀነሰው የግብይት መፈፀሚያ የክፍይ መጠን: | የተቃጠለው የቶክኖች ብዛት |
|---|---|---|
| **10K $ETN** | **100 $ETN (1%)** | **50 $ETN** (50% of the fee) |
| ቀሪ የግብይት መፈፀሚያ ክፍያ | ለተቀባዩ የሚደርሰው የቶክን መጠን | ከአጠቃላይ የቶክኑ አቅርቦት ላይ የሚቀነሰው የቶክን ብዛት |
| **50 $ETN** | **9,900 $ETN** | **50 $ETN** |

በዚህም በዚህ የቶክን ዝውውር ተቀባዩ አካል 9,900 የ$ETN ቶክኖችን የሚቀበል ሲሆን 50 የ$ETN ቶክኖች የሚቃጠሉ እና ከስርዓቱ ውጪ የሚሆኑበት ቀሪው 50 የ$ETN ቶክኖች ደግሞ እንደግብይት መፈፀሚያ ክፍይ የሚውል ይሆናል ማለት ነው።

©etnetsa apps , 2024
All Rights Reserved

© Identico, 2024
All Rights Reserved

Identico®
Mickey Leland St.
Bole Atlas, Isabella Building, 3rd Floor
Addis Ababa, Ethiopia
Contact Us
+251 96 556 4436
identicostudio@gmail.com

# 8. መደምደሚያ

ET Netsa Coin ($ETN) ቶክን ከዲጂታል እሴትነትም ያለፈ ትልምን ይዞ የተነሳ፤ በኮሚዩኒቲው እና በአጠቃላይ አባላቱ ጥቅም እና አገልግሎት ላይ ዋናውን ትኩረቱን አድርጎ የሚንቀሳቀስ፡ እንዲሁም እጅግ በጣም ተለዋዋጭ በሆነው የክሪፕቶ ከረንሲ ግብይት አለም አባላት የሚማሩበትን፤ ራሳቸውን ችለው ገንዘብ የሚያገኙበትን ሁነት ለመፍጠር ዋነኛ አላማው አድርጎ የተነሳ ፕሮጀክት ነው። ጠንካራ የሆነ ኮሚዩኒቲን በመመስረት እና ትክክለኛ እውቀት ላይ የተመሰረቱ፤ የሪክስ ማኔጅመንትን ትኩረት ሰተው በሚዘጋጁ የገበያ ጥናቶች አባላት ህይወታቸውን መለወጥ የሚችሉበትን፤ ሁሉም በእኩል የሚታዩበትን እና በእኩልም የሚጠቀሙበትን ሁነት ምህዳር መፍጠር ዋና ግቡ በማድረግ የተቀረፀም ፕሮጀክት ነው።.

ይህንን አስደናቂ እና ይበል የሚያሰኝ በአይነቱ በአገራችን የመጀመሪያ የሆነውን ፕሮጀክት ተቀላቀሉ። በጉዟችን የሚኖሩንን እንቅፋቶች እንደመማሪያ፤ የምናገኛቸውን ትሩፋቶች ደግሞ እንደህይወት መቀየሪያ እንጠቀማቸው ዘንድ የኮሙዩኒቲው ቤተሰብ ትሆኑ ዘንድም ተጋብዛቹሀል። ለበለጠ መረጃ ትክክለኛውን የቴሌግራም ቻናላችንን አልያም ድህረገፃችንን ትመለከቱ ዘንድም ለማስታወስ ወደድን።
እናመሰግናለን።

©etnetsa apps , 2024
All Rights Reserved

© Identico, 2024
All Rights Reserved

Identico®
Mickey Leland St.
Bole Atlas, Isabella Building, 3rd Floor
Addis Ababa, Ethiopia

Contact Us
+251 96 556 4436
identicostudio@gmail.com